የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሰላሳኛ ዓመት ቁጥር ፴፯
አዲስ አበባ ሰኔ ፲፰ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

30th Year No.37
ADDIS ABABA 25th June, 2024

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፳፯/፪ሺ፲፮

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በኢንዶኔዥያ መንግሥት መካከል የዲፕሎማቲክ እና ሰርቪስ ፓስፖርት ለያዙ ሰዎች ቪዛን ለማስቀረት የተፈረመውን ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ…ገጽ ፲፭ሺ፮፻፹፭

**Content**

Proclamation No.1327/2024

Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Indonesia on Visa Exemption for Holders of Diplomatic and Service Passports Ratification Proclamation……......................Page 15685

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፳፯/፪ሺ፲፮

## በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በኢንዶኔዥያ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የዲፕሎማቲክ እና ሰርቪስ ፓስፖርት ለያዙ ሰዎች ቪዛን ለማስቀረት የተደረገው ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በኢንዶኔዥያ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የዲፕሎማቲክ እና ሰርቪስ ፓስፖርት ለያዙ ሰዎች ቪዛን ለማስቀረት የተደረገ ስምምነት መስከረም ፲፪ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም በኒውዮርክ ከተማ የተፈረመ በመሆኑ፤

## Proclamation No.1327/2024

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF THE REPUBLIC OF INDONESIA ON VISA EXEMPTION FOR HOLDERS OF DIPLOMATIC AND SERVICE PASSPORT

**WHEREAS,** the Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Indonesia on Visa Exemption for Holders of Diplomatic and Service Passports was signed in New York ,on the 23rd day of September 2019;

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

ይህንኑ ስምምነት የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ግንቦት ፳፪ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም በአካሄደው ፳፱ኛ መደበኛ ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

፩.አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በኢንዶኔዥያ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የዲፕሎማቲክ እና ሰርቪስ ፓስፖርት ለያዙ ሰዎች ቪዛን ለማስቀረት የተፈረመውን ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፩፫፻፳፯/፪ሺ፲፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

፪.የስምምነቱ መጽደቅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በኢንዶኔዥያ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል መስከረም ፲፪ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም የዲፕሎማቲክ እና ሰርቪስ ፓስፖርት ለያዙ ሰዎች ቪዛን ለማስቀረት በኒውዮርክ፣አሜሪካ የተፈረመው ስምምነት በዚህ አዋጅ ጸድቋል::

፫.አስፈፃሚ አካል

የኢፌዲሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር

WHERE AS, the House of People's Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia approved the said agreemnt in its 29th regular meeting held on 30th May 2024;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 sub-Articles (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Indonesia on Visa Exemption for Holders of Diplomatic and Service Passports Ratification Proclamation No.1327/2024".

2. Ratification of the Agreement

The Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Indonesia on Visa Exemption for Holders of Diplomatic and Service Passports signed in New York, USA on 23rd September 2019 is hereby ratified by this proclamation.

3. Implementing Organ

The Ministry of Foreign Affairs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia in

ይህንን ስምምነት የማስፈጸም ኃላፊነት በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል::

፬.አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል::

አዲስ አበባ ሰኔ ፲፰ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም

ሣህለ ወርቅ ዘውዴ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

collaboration with the relevant government organs is hereby empowered to implement this Agreement.

4. **Effective Date**

This Proclamation shall come into force upon publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, on this 25th day of June, 2024

SAHLE WORK ZEWDE

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA